# ውጤቶችና ቢነሱ የሚባሉ ጥያቄዎች

ይህ አባሪ 35ቱን ውጤቶች (Outcomses)ና አስተባባሪዎች በቡድናቸው ውስጥ ውይይትን ለማሳለጥ ቢያነሱዋቸው ይጠቅማሉ የሚባሉ ጥያቄዎችን ዝርዝር ይዟል። እነዚህን ጥያቄዎች መጠቀም ግዴታ እንዳልሆነና ሌሎችን መንገዶችን መጠቀም እንደምትችሉ አትርሱ።

**<u>አስፈላጊ ማስታወሻ!</u>** በሁሉም ሁኔታ ተማሪዎች የተማሩትን ለእነርሱ አካባቢ በሚስማማ መልኩ መተግበር መቻል አለባቸው።በፕሮግራሙ መጨረሻ ለእያንዳንዱ ተማሪ የተሞላ የግምገማ ቅጽ (አባሪ "ለ"ን ይመልከቱ) በቅጹ ላይ በተጠቀሰው አድራሻ ላኩ።

**ሁሉም ውጤቶች የሚጀምሩት እና የሚጨርሱት "ተማሪዎች ...ለማድረግ ይችላሉ።" ብለው ነው።**

| ውጤቶች | ቢነሱ የሚባሉ ጥያቄዎች |
|---|---|
| **1. ቃሉን ማወቅ**<br>ብዙ ጊዜ መጽሀፍ ቅዱሳዊ ስነ መለኮት ተብሎ ይጠራል፤የብሉይ ኪዳን እና የሀዲስ ኪዳን ዳሰሳ ነው። | |
| 1.1. በብሉይ ኪዳን ውስጥ ካሉት ዋና ዋና ክስተቶች 10ሩን ተናገሩና ቢያንስ የ10 የብሉይ ኪዳን ዋና ዋና ሰዎችን ታሪክ አካፍሉ። | ዳግም ለተወለደ አዲስ ክርስቲያን ብሉይ ኪዳንን የማወቅን ጥቅም 10 ክስተቶችንና 10 ሰዎችን በመጠቀም አስረዱ። |
| 1.2. 5 ምሳሌዎችን በመጠቀም ኢየሱስ እንዴት የብሉይ ኪዳንን ትንቢቶች እንዳሟላ አስረዱ። | አዲስ ኪዳን ለምን ኢየሱስ የብሉይ ኪዳንን ትንቢቶች ማሟላቱን እንደሚያረጋግጥ ላልገባው፣ ከብሉይ ኪዳንም ይሄንን ፈልጎ ማረጋገጥ ጊዜን የሚፈጅ ጉዳይ ለሆነበት አንድ የቤተክርስቲያን አባል የተለያዩ ምሳሌዎችን በመጠቀም እንዲህ ያሉ ዝርዝሮችን ማጥናትና ማወቅ እንዴት እንደሚረዳንና እምነታችንን እንደሚያሳዳግ አስረዱ። |
| 1.3. ቢያንስ ለ5 የኢየሱስ ዋና አስተምህሮዎች ማጠቃለያ ስጡ። | አንድ ምክርን የሚፈልግ የቤተ ክርስቲያን አባል ለመምከር ወይም ለማበረታታት እያንዳንዱን የኢየሱስ ዋና አስተምህሮ እንዴት እንደምትጠቀሙበት ምሳሌ ስጡ። |
| 1.4. የኢየሱስ ሞትና ትንሳኤ ለምን በጣም አስፈላጊ እንደሆነ አስረዱ። | ኢየሱስ ሁሌም ድል አድራጊ የሆነ ነቢይ ብቻ ነው ብሎ ለሚያምን አንድ ሙስሊም ጓደኛችሁ ኢየሱስ ለምን መሞት እንደነበረበትና ይሄ ደግሞ በትንሳኤው በኩል ለምን የድል መንገድ እንደሆነ አስረዱ። |

| ውጤቶች | ቢነሱ የሚባሉ ጥያቄዎች |
|---|---|
| 1.5. ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የነበረውን ግንኙነት ዛሬ ሌሎችን ደቀ መዝሙር ለማድረግ እንዴት እንደሚጠቅም አስረዱ። | ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የነበረውን ግንኙነት መርሆች በአጥቢያ ቤት ክርስቲያናችሁ ውስጥ እንዴት ተግባራዊ ታደርጋላችሁ? |
| 1.6. በሐዋሪያት ስራ መጽሀፍ ላይ የተጠቀሱ 10 ዋና ዋና ክስተቶችን ግለጹ። | በሐዋሪያት ስራ መጽሀፍ ላይ የተጠቀሱት እነዚህ ክስተቶች ለቤተ ክርስቲያናችሁ ታሪክ ምን እንደሚጠቅሙ አስረዱ። |
| 1.7. ቢያንስ ሶስት የጳውሎስን ቁልፍ አስተምህሮዎች አስረዱ። | እነዚህ የጳውሎስ አስተምህሮዎች ለግል መንፈሳዊ ህይወታችሁ እንዴት እንደረዷችሁ አስረዱ። |
| **2. በእምነት መኖር**<br>ብዙ ጊዜ ተግባራዊ ስነ መለኮት፣ ስነ አፈታት፣ የህጻናት አገልግሎት፣ የቤተ ክርስቲያን አመራር፣ ግንኙነቶች ተብሎ ይጠራል። | |
| 2.1. ውጤታማ ስብከት መስበክ ወይም ማስተማር። | በእናንተ አመለካከት ካስተማራችሁት ወይም ከሰበካችሁት ምርጡ መልዕክት የቱ ነበር? ደካማው መልዕክትስ የቱ ነበር? ለመልሳችሁ ማብራሪያ ስጡ። |
| 2.2. ለአንድ ቡድን አንድን የመጽሀፍ ቅዱስ ምንባብ በግልጽ አስረዱ። | የመጽሀፍ ቅዱስ ክፍልን አብራርታችሁ ክርስቲያን ወገኖች በደንብ እንዲረዱትና እንዲኖሩት የረዳችሁባቸውን ሁለት ጊዜያት አስታውሱ። ለምን ነበር በጣም ውጤታማ የሆኑት? |
| 2.3. የመንፈስን ፍሬ በሁሉም የህይወት አቅጣጫ አፍሩና ትህትናን፣ ታማኝነትንና ያልተወሳሰበ ህይወት መኖርን ተለማመዱ። | በአዲስ ኪዳን በተገለጹት የመንፈስ ፍሬዎችና በአከባቢያችሁ ባለው ባህልና ማህበረሰብ መካከል ከፍተኛ ልዩነት የምታዩት ምን ላይ ነው? |
| 2.4. መንፈሳዊ ልምምዶችን ዘርዝሩ፣አስረዱ እና ተለማመዱ። | ከመንፈሳዊ ልምምዶች ውስጥ በጣም የሚያታግሏችሁ ሁለቱ የትኞቹ ናቸው? ለማስተካከል ምን እያደረጋችሁ ነው? |
| 2.5. ከጉባኤ ጋር በሚኖር ግንኙነት መጽሀፍ ቅዱሳዊ ስነምግባርን አሳዩ። | ለጉባኤያችሁ ደህና መሆንና ወደፊት እድገት ጠቃሚ የሆኑ ሶስት ስነ ምግባራዊ እሴቶችና መርሆችን ዘርዝሩ።ለምን እንደሆነም አስረዱ። |

| ውጤቶች | ቢነሱ የሚባሉ ጥያቄዎች |
|---|---|
| 2.6. በሁሉም ግንኙነቶች ልዩ ፍላጎት ያላቸው ሰዎች ጋር ያለ ግንኙነትን ጨምሮ ርህራሄን፣እንግዳ ተቀባይነትንና ይቅርታን አሳዩ። | "ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ" ሲል ምን ማለቱ ነው? ለምንድነው ኢየሱስ እና መጽሀፍ ቅዱስ ከፍተኛ ትኩረት የሰጡት? የአንድ ሰውን አካል ጉዳት ወይም አስጨናቂ ሁኔታ እንደ ምሳሌ ተጠቀሙ። |
| 2.7. መልካምነትን እና እንግዳ ተቀባይነትን ተለማመዱ። | አንዲት የቤተ ክርስቲያን አባል ለሌሎች ቀጥታ መመስከርና መስበክ ብቸኛው መጽሀፍ ቅዱሳዊ መንገድ እንደሆነና ሌላው ሁሉ ጊዜ ማባከን እንደሆነ ገለጸች።መጽሀፍ ቅዱሳችሁን ተጠቅማችሁ መልካምነትና እንግዳን መቀበል ጊዜን ማባከን እንዳልሆነ ይልቁንም የወንጌል ምስክርነት ነው ብላችሁ ተከራከሩ። |
| **3. ሌሎችን መድረስ**<br>በተለምዶ የወንጌል ስርጭት፣የተልዕኮ ስራ፣ደቀ መዛሙርትን ማፍራት ተብሎ ይጠራል። | |
| 3.1. ሌሎችን ለተልዕኮ ማነሳሳት። | አማኞችን በተልዕኮ ስራ ድርሻ እንዲኖራቸው የምትጠይቁበት ንግግር አዘጋጁ።መጽሀፍ ቅዱስን መነሻ አድርጋችሁ ተጠቀሙ። |
| 3.2. ወንጌልን ለቤተሰባችሁ፣ለጓደኞቻችሁ እና ለእንግዳ ሰዎች በውጤታማነት አካፍሉ። | ወንጌልን በግል እና በጋራ ማካፈልን በተመለከተ በቤተ ክርስቲያናችሁ እና በባህላችሁ ላይ የምታዩት አንድ ወይም ሁለት ዋና ተግዳሮቶች ምንድናቸው? ከነዚህ ተግዳሮቶች የተነሳ የማይመሰክሩ ሰዎችን እንዴት ልታርሟቸው እንደምትችሉ አስረዱ። |
| 3.3. ቢያንስ አንድን ሰው በተለየ ሁኔታ ለወንጌል ስርጭት ወይም ለተልዕኮ ስራ አብቁ። | አንድን ሰው ለወንጌል ስርጭትና ከተልዕኮ ስራ ጋር በተገናኘ ልዩ ስጦታውን እንዲያዳብር እንዴት በውጤታማነት እንዳማከራችሁ እና ደቀ መዝሙር እንዳደረጋችሁ አስረዱ። |
| 3.4. መጽሀፍ ቅዱስ ከባህል በላይ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ አብራሩ። | ባህላችሁ እና በዙሪያችሁ ያለው ማህበረሰብ መጽሀፍ ቅዱሳዊ እሴቶችንና መመዘኛዎችን ቢሰሙና ቢከተሉ በደንብ የሚያተርፉባቸውን ሶስት ምሳሌዎች ዘርዝሩ። |

| | ውጤቶች | ቢነሱ የሚባሉ ጥያቄዎች |
|---|---|---|
| 3.5. | ቴክኖሎጂንና የማህበራዊ ትስስር ገጾችን ለአገልግሎት ተጠቀሙ። | በአከባቢያችሁ በጣም ውጤታማው ቴክኖሎጂ/ የማህበራዊ ትስስር መሳሪያ የቱ ነው?ለምን? እናንተ እና ቤተ ክርስቲያናችሁ በሙያዊ ብቃት በታገዘ መልኩ ለመጠቀም ምን ያህል እየሰራችሁ ነው? |
| 3.6. | አገልጋይ መሪነትን አሳዩ። | በቤተ ክርስቲያናችሁ ላለ የቤተ ክርስቲያን መሪ ሊከበርና ሌሎች ሊያገለግሉት ይገባል ብሎ ለሚያስብ አንድ ሰው ኢየሱስ ለምን በተለየ ሁኔታ እንደኖረ እና ይህም ከክርስቲያናዊ የቤተክርስቲያን አመራር ተዋረድ አንጻር ለምን አስፈላጊ እንደሆነ አስረዱ። |
| 3.7. | በሆነ አይነት የቤተ ክርስቲያን አመራር ውስጥ ገብተው እንዲያገለግሉ ቢያንስ 3 ሰዎችን ለዩና አሰልጥኑ። | አንድን ሰው የአመራር ክህሎቱን እንዲያዳብር የረዳችሁባቸውን ሶስት መንገዶች ዘርዝራችሁ አብራሩ። |
| **4.** | **መስማት እና ማበረታታት**<br>ብዙ ጊዜ ማማከር እና ቤተሰብ ይባላል። | |
| 4.1. | ሌሎችን በጭንቀታቸው ወቅት ማለትም ሞት፣ የጋብቻ ችግር፣ ህመም የመሳሰሉት ሲያጋጥሟቸው እርዷቸው እና አስተዛዝኗቸው። | ሰዎችን በከባድ ጭንቀት ውስጥ ሆነው ልትረዷቸው የቻላችሁባቸውን ሶስት ጉዳዮች አስረዱ። |
| 4.2. | ጥንዶች ለትዳር ሲዘጋጁ፣ በለቅሶ ወቅት፣ በጋብቻ ችግር፣ በህመም ወይም በመሳሰሉት እርዷቸው። | በእናንተ ባህል ትዳር ሲመሰረት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሶስት ዋና ዋና ችግሮች ምንድናቸው? እባካችሁ ለምን እንደሆነ አስረዱ። |
| 4.3. | በመጽሀፍ ቅዱስ ላይ እግዚአብሔር ልጆችን የተጠቀመበትን 7 ታሪኮችን ዘርዝሩ። | አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችሁን ልጆችን በተመለከተ ማንቃት ቢኖርባችሁ የትኞቹን ሁለት ታሪኮች ትሰብካላችሁ? ለምን? |
| 4.4. | ኢየሱስ ለልጆች ያለው አመለካከት እንዴት ቤተ-ክርስቲያንን ሊለውጥ እንዳለበት አብራሩ። | ኢየሱስ ለልጆች ያለውን አመለካከት<br>ሀ) ከባህላችሁና<br>ለ) ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችሁ ጋር አነጻጽሩ። ሁለት ተመሳሳይ ነገሮችንና ሁለት ከኢየሱስ ባህላችሁ እና ቤተ ክርስቲያናችሁ መማር የሚገባቸውን ነገሮች ዘርዝሩ። |

| | ውጤቶች | ቢነሱ የሚባሉ ጥያቄዎች |
|---|---|---|
| 4.5. | ከልጆች እና ከታዳጊ ወጣቶች ጋር በአገልግሎት ተሳትፎ ማድረግ። | በቤተ ክርስቲያናችሁ ከህጻናት ጋር ወይስ ከአዋቂዎች ጋር መስራት ይቀላችኋል? ይሄ ለምን እንደሆነና ምርጫችሁ ከየት እንደመነጨ (ከቤተሰብ፣ከመሳሰሉት) አብራሩ። |
| 4.6. | በቤተሰብ እና በትዳር ውስጥ ታማኝነትንና ፍቅርን ማዳበር። | የትዳር መንፈሳዊ ሁኔታና በእናት እና በአባት መካከል ያለው ግንኙነት በልጆች አስተዳደግ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንዳለው ሶስት ምክንያቶችን ጥቀሱ። |
| 4.7. | የአባቶችን አለመኖር ተጽዕኖ ግለጹ። | በስራ፣ በማህበረሰብ ውስጥ፣ በፖለቲካ ወይም በቤተ ክርስቲያን ንቁ ተሳታፊ መሆን ከልጆቹ ጋር ከመሆን እነርሱን ከመምከር እና ከማስተማር ይልቅ አስፈላጊ ነው፤ ዞሮ ዞሮ ይሄንን ሚስቴ ከእኔ የተሸለ ታደርገዋለች የሚል አቋም ከያዘ አንድ የቤተ ክርስቲያን አባል ጋር እንዴት ብላችሁ ትከራከራላችሁ? |
| **5. እምነት የሚጣልበት እምነት** ብዙ ጊዜ ስልታዊ ስነ መለኮት ፣ስነ ምግባር፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ ባለአደራነት። | | |
| 5.1. | በትክክለኛ አስተምህሮ ማመን እና መለማመድ። | ትክክለኛ አስተምህሮ ለምን ያስፈልጋል? |
| 5.2. | የአዲስ ኪዳንን ቁልፍ አስተምህሮዎች ጠቅለል አድርጋችሁ አብራሩ። | በእናንተ አመለካከት ዳግመኛ የተወለደ አዲስ ክርስቲያን በተቻለ ፍጥነት ሊረዳቸውየሚገቡ ዋና ዋና አስተምህሮዎች የትኞቹ ናቸው ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን? |
| 5.3. | በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ 3ቱን በጣም አስፈላጊ ክስተቶች አስረዱ። | አንድ ክርስቲያን መጽሀፍ ቅዱስን ብቻ ማወቅ ብቻ በቂዬ ነው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አይስበኝም ቢል እንዴት ምላሽ ትሰጣላችሁ? መጠናት ወደሚገባው ወደ የትኛው ሰው ወይም ታሪክ ትጠቁሙታላችሁ?ለመልሶቻችሁ ምክንያት ስጡ። |
| 5.4. | ቤተ እምነታችሁ (የቤተ ክርስቲያናችሁ እንቅስቃሴ) እንዴት እንደተጀመረ ግለጹ። | ለአንድ አማኝ ጥሩ ምሳሌ መስጠት ከፈለጋችሁ ከቤተ እምነታችሁ እና ከቤተ ክርስቲያናችሁ መስራቾች መካከል ማንን ትመርጣላችሁ? ይህ ሰው ለሌሎች የእምነት አርአያ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው? |

| | ውጤቶች | ቢነሱ የሚባሉ ጥያቄዎች |
|---|---|---|
| 5.5. | ስለባለአደራነት፣ ስለመስጠትና ስለመባ መጽሀፍ ቅዱሳዊ መሰረቱን አብራሩ። | መጽሀፍ ቅዱሳችሁን በመጠቀም አማኞች በልግስና ለአገልግሎት እንዲሰጡ የሚያሳስቡ 5 የአዲስ ኪዳን ምንባቦችን አሳዩ። |
| 5.6. | የብልጽግና ወንጌል ለምን መጽሀፍ ቅዱሳዊ እና ስነ ምግባራዊ እንዳልሆነ አስረዱ። (ማስታወሻ፡ በአከባቢያችሁ የብልጽግና ወንጌል ችግር ካልሆነ ዋና ጉዳይ የሆነውን ምረጡ።) | ቤተ ክርስቲያናችሁን ለቆ በህይወት የበለጠ ስኬታማ ለመሆን ተስፋ በማድረግ የብልጽግና ወንጌል ሰባኪ ቤተ ክርስቲያን ለመካፈል ለፈለገ አንድ የቤተ ክርስቲያናችሁ አባል ሶስት መጽሀፍ ቅዱሳዊ ማብራሪያዎችን አቅርቡ። |
| 5.7. | የቤተ ክርስቲያንን ጥቅም ግለጹ። | በቤተ ክርስቲያናችሁ ኢየሱስን ለሚወድ ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ካሉ ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር መሰባሰብ ሸክም መስሎ የተሰማውአንድ ሰው አለ።ቤቱ መቀመጥ እንደሌለበት ለማሳመን እንዴት ታስረዱታላችሁ? |